ትምህርት 59

1. ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን (ጸሐፍት) በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ላይ የተቆጡት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የአባቶችን ወግ ስላልጠበቁ ነበር።

2. የአባቶች ወግ ምን ነበር?

ሀ- እነዚህ ወጎች ፈሪሳውያኑ ራሳቸው የፈጠሩአቸው ወጎች ሲሆኑ፣ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት እነዚህን ወጎች መጠበቅ አለባቸው ይሉአቸው ነበር።

3. ከምንጠብቃቸው ወጎች የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላልን?

ሀ- አንችልም።

4. ወጎችን መጠበቅ ልብን ያነጻል?

ሀ- አያነጻም::

5. ኢየሱስ ፈርሳውያንን ግብዝ አላቸው። ግብዝ ምንድን ነው?

ሀ- ግብዝ ንግግሩና ተግባሩ የማይስማማና ሙሉ በሙሉ የተለያየ ሰው ነው።

6. ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ እነዚህ ሰዎች የተናገረው ምን ነበር?

ሀ- ነቢዩ ኢሳይያስ "ሕዝቡ በአፉ በእግዚአብሔር እናምናን ይላሉ ልቡ ግን ከእግዚአብሔር የራቀ ነው" አለ።

7. እግዚአብሔር የፈሪሳውያንን አምልኮ ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም የእነርሱ አምልኮ ከአፋቸው ብቻ እንጂ ከልባቸው ስላልሆነ ነበር።

8. እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ መጽሐፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሳቸውን ወጎች እንዲጨምሩ ይፈልጋል?

ሀ- አይፈልግም።

ለ- እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት በተናገረው ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ የለብንም።



9. ሰዎች ባልታጠቡ እጆች ወይም በረከሰ ምግብ ምክንያት የማይረከሱት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ያልታጠበ እጅና የረከሰ ምግብ ልብን መንካት ስለማይችሉ ነው።

10. በምንበላው ወይም ሳንበላ በተውነው ምግብ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?

ሀ- አናገኝም።

11. በምንለብሰው ወይም ሳንለብስ በተውነው ልብስ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?

ሀ- አናገኝም።

12. ኢየሱስ ሰውን የሚያረክሰው ምንድን ነው አለ?

ሀ - ሰውን የሚያረክሰው ከውስጥ የሚወጣ ነገር ነው አለ።

13. በልባችን ያሉት ክፋቶች ምን ምንድን ናቸው?

ሀ- ክፉ አሳብ ዝሙት ሌብነት ሰው መግደል ማመንዘር ስግብግብነት ክፋት ማታለል መዳራት ምቀኝነት ስም ማጥፋት ትዕቢት ስንፍና ናቸው።

14. ኢየሱስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ ወደ ቤተ መቅደስ ሊጸልዩ የሄዱ ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ?

ሀ- አንደኛው ፈሪሳዊ ሲሆን፣ ሌላኛው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር።

15. እግዚአብሔር ፈሪሳዊውን ያልተቀበለው ለምን ነበር?

ሀ- ፈሪሳዊው ልቡ ንጹህ ያለመኑን አምኖ ስላልተቀበለ።

ለ- ፈሪሳዊው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላላመነ።

16. እግዚአብሔር ቀረጥ ሰብሳቢውን የተቀበለው ለምን ነበር?

ሀ- ቀረጥ ሰብሳቢው ንጹህ ያልሆነ ልብ እንዳለው ስላወቀ።

ለ- ቀረጥ ሰብሳቢው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላወቀ።

ሐ- ቀረጥ ሰብሳቢው እንዲያድነው የእግዚአብሔርን ስም ስለጠራ።

- አንድ ቀን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው።

ማርቆስ 8:27-28

27- ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ መንደሮች ሄደ፤በመንገድ ላይ ሳሉም ደቀ መዛሙርቱን "ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል" ብሎ ጠየቃቸው።

28- እነርሱም "መጥምቁ ዮሐንስ የሚሉህ አሉ፤ ሌሎች ኤልያስ ነው ይሉሃል ሌሎች ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" ብለው ነገሩት።

- ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቃቸው ጥያቄ ምን ነበር?

- "ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል" ብሎ ጠየቃቸው።

- ደቀ መዛሙርቱ ምን ብለው መለሱለት?

- አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ብለው ያስባሉ።

- ሌሎች ኢየሱስ ኤልያስ ነው በለው ያስባሉ።

- ሌሎች ኢየሱስ ከነቢያት አንዱ ከሞት ተነስቶ ነው ይላሉ አሉት።

- ሰዎች ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ብለው ያሰቡት ለምን ነበር?

- ንጉስ ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ገድሎት ስለነበር አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስን መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነስቶ ነው ብለው ያስቡ ስለነበር።

- ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ነበር?
- አልነበረም::

- ሰዎች ኢየሱስ ኤልያስ ነው ብለው ያሰቡት ለምን ነበር?

- ኤልያስ ማን ነበር?

- ኤልያስ ሳይሞት በእግዚአብሔር ወደ ሰማይ የተወሰደ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው።

- ኢየሱስ ኤልያስ ነበር?
- አልነበረም::

- ሰዎች ኢየሱስ ከነቢያት አንዱ ከሞት ተነስቶ ነው ብለው ያሰቡት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ነቢያት ሁልጊዜ ስለ እግዚአብሔር የሚናገሩና ሕዝቡን ለንስሐ የሚጠሩ ስለነበሩ ነው።

- ኢየሱስ ከሞት የተነሣው የብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢይ ነው?

- አይደለም::

- ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቃቸው ጥያቄ ምን ነበር?

ማርቆስ 8:29

29- ቀጥሎም "እናንተሳ ማን ትሉኛላችሁ?" ሲል ጠየቃቸው። ጴጥሮስም "አንተ ክርስቶስ ነህ" አለው።

- ቀጥሎም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ምን ጠየቃቸው።

- "እናንተሳ ማን ትሉኛላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው።

- ጴጥሮስ ምን ብሎ መለሰለት?

- "አንተ ክርስቶስ ነህ" አለው።

- ጴጥሮስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን በዔድን የአትክልት ስፍራ ቃል ኪዳን የገባላቸው ክርስቶስ መሆኑን አውቋል።

- ጴጥሮስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል የገባላቸው ክርስቶስ መሆኑን አውቋል።

- ጴጥሮስ ኢየሱስ ክርስቶስና አዳኙ እግዚአብሔር እንደሆነ አውቋል።

- ኢየሱስ እርሱ አዳኝ አምላክ መሆኑን ብዙ ጊዜ ቢነግራቸውም ብዙ አይሁዶች አላመኑም።

- ኢየሱስ ብዙ ተአምራት በአይሁድ ፊት ቢሠራም ብዙ አይሁዶች ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አላመኑም ነበር።

- እኛ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ካላመንን መዳን እንችላለን?

- አንችልም።

- ቀጥሎስ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አላቸው?

ማርቆስ 8:30

30- ኢየሱስም ስለእርሱ ለማንም እንዳይናገሩ አስጠነቀቃቸው።

- ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ስለእርሱ ለማንም እንዳይናገሩ ያስጠነቀቃቸው ለምን ነበር።

- ኢየሱስ ሰዎች ለሌላ ሰው ብለው እንዲያምኑበት ስላልፈለገ ነው::

- ኢየሱስ ሰዎች ከልባቸው እንዲያምኑበት ይፈልጋል።

- በኢየሱስ ካመንን ይህ እምነት ከልባችን የመነጨ መሆን አለበት።

- ለሌላ ሰው ብለን በኢየሱስ ማመን አንችልም።

- ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ለደቀ መዛሙርቱ አስተማራቸው።

ማርቆስ 8፥31

31-ከዚያም ኢየሱስ የሰው ልጅ ብዙ መከራ እንደሚቀበል፥ በሽማግሌዎች፥ በካህናት አለቆችና በጸሓፍት እንድሚናቅ፥ እንደሚገደል፥ ከሶስት ቀንም በኋላ እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር።

- ኢየሱስ ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ለደቀ መዛሙርቱ ምን አስተማራቸው?

- የሕዝቡ መሪዎች እርሱን እንደሚገድሉት ነገር ግን በሶስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሣ።

- ኢየሱስ ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች በምን አወቀ?

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ሁሉን ነገር ያውቃል።

- ኢየሱስ የማያውቀው ምንም ነገር የለም።

- ኢየሱስ የሕዝቡ መሪዎች እንደሚገድሉት ያውቃል።

- ኢየሱስ እንደሚሞት ያውቃል።

- ይሁን እንጂ ኢየሱስ በሶስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሣም ያውቃል።

- ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ውስጥ ለምን ያህል ቀናት እንደቆየ ታስታውሳላችሁ?

- ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት።

-ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት እንደቆየ ኢየሱስ በምድር ከርስ ውስጥ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት አሳልፎአል።

- እግዚአብሔር ዮናስን ከዓሣ አንባሪ ሆድ ውስጥ ከሶስት ቀንና ከሶስት ሌሊት በኋላ እንዳወጣው ሁሉ ኢየሱስንም ከሶስት ቀንና ከሶስት ሌሊት በኋላ ከሞት አስነስቶታል።

- ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ወደ አንድ ትልቅ ተራራ ሄደ።

ማርቆስ 9፡2-3

2- ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ፥ ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ አንድ ረጅም ተራራ ይዞአቸው ወጣ፤ ብቻቸውንም ነበሩ፤ በፊታቸውም ተለወጠ፤

3- ልብሱም በምድር ማንም አጣቢ አጥቦ ሊያነጣው በማይችልበት ሁናቴ እጅግ ነጭ ሆነ።

- ኢየሱስ በተራራ ላይ ምን ሆነ?

- ኢየሱስ በጴጥ በያዕቆብንና በዮሐንስ ፊት ተለወጠ።

- ኢየሱስ ተለወጠ ማለት ምን ማለት ነው?

- በኢየሱስ ውስጥ ያለው መለኮታዊነት ወደ ውጭ አንጸባረቀ ማለት ነው።

- አኢየሱስ በውጭ ሰብዓዊ አካል ቢኖረውም በውስጥ አምላክ ነው።

- ሙሴና እስራኤላውያን በምድረ በዳ ስለሠሩት የመገናኛ ድንኳን ታስታውሳላችሁ?

- በውጭ በኩል ድንኳኑ በእንስሳት ቆዳዎች የተሠራ ሲሆን በውስጥ በኩል ግን የእግዚአብሔር ክብር ነበረው።

- ሰዎች ኢየሱስን በሚያዩበት ጊዜ የሚመለከቱት ውጫዊ አካሉን ብቻ ነው።

- በውስጥ በኩል ግን ኢየሱስ አምላክ ነበር።

- ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹምም ሰው ነበር።

- በድንገት ሁለት ሰዎች ከኢየሱስ አጠገብ ታዩ።

ማርቆስ 9፡4

4- ኤልያስና ሙሴም ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።

- ኤልያስ ማን ነበር?

- ኤልያስ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት በምድር ላይ ይኖር የነበረ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው።

- ከብዙ ዓመታት በፊት ኤልያስ ሳይሞት እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ወሰደው።

- ሙሴ ማን ነበር?

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ምድር መርቶ ያወጣ ሰው ነበር።

- ከብዙ ዓመታት በፊት ሙሴ ሞተ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ሰማይ ወሰደው።

- ኤልያስና ሙሴ በእግዚአብሔር ስላመኑ በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ለብዙ ዓመታት ይኖሩ ነበር።

-ኤልያስና ሙሴ ወደ ምድር የተመለሱት እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር አብ ኤልያስና ሙሴ ከኢየሱስ ጋር እንዲነጋገሩ ከሰማይ ወደ ምድር ላካቸው።

- እግዚአብሔር ኤልያስና ሙሴ ከኢየሱስ ጋር እንዲነጋገሩ ለምን ፈለገ?

- ኢየሱስ ሊሞት ስለሆነ ኤልያስና ሙሴ እንዲያበረታቱት ስለፈለገ።

- ቀጥሎስ ምን አለ?

ማርቆስ 9፡5-8

5- ጴጥሮስም ኢየሱስን “መምህር ሆይ፤እዚህ ብንኖር ለእኛ መልካም ነው፤አንድ ለአንተ፥ አንድ ለሙሴ፥አንድ ለኤልያስ የሚሆኑ ሶስት ዳሶች እንሥራ” አለው።

6- እጅግ ስለፈሩ የሚናገረውን አያውቅም ነበር።

7- ከዚያም ደመና መጥቶ ጋረዳቸው ከደመናውም ውስጥ “ይህ የሚወደው ልጄ ነው እርሱን ስሙት!” የሚል ድምጽ መጣ።

8- ወዲያውም ዙርያቸውን ሲመለከቱ ከኢየሱስ በቀር ማንም አብሮአቸው አልነበረም።

- ከደመና ውስጥ የመጣው ድምጽ የማን ነበር?

- የእግዚአብሔር አብ።

- እግዚአብሔር አብ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አላቸው?

- "ይህ የሚወደው ልጄ ነው እርሱን ስሙት!" አለ።

- እግዚአብሔር አብ ምን ማለቱ ነበር?

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን እጅግ እንደሚወደውና እርሱም እውነተኛ አዳኝ አምላክ መሆኑን መናገሩ ነበር።

- ኢየሱስ አዳኙ አምላክ ስለሆነ እግዚአብሔር ደቀ መዛሙርት እንዲያደምጡት ይፈልጋል።

- ዛሬ እግዚአብሔር ከሰማይ ይናገረናል?

- አይናገረንም።

-ለምን?

-ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊነግረን የሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈዋል።

- እግዚአብሔር በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉትን የኢየሱስንና የእርሱን ቃል እንዲናደምጥ ይፈልጋል።